የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

# ፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ

# FEDERAL NEGARIT GAZETTE

## OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

ሃያ ሰባተኛ ዓመት ቁጥር ፲፭
አዲስ አበባ የካቲት ፲፪ ቀን ፪ሺ፲፫ ዓ.ም

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

27th Year, No.15
ADDIS ABABA 19th February, 2021


**ማውጫ**


አዋጅ ቁጥር ፩ሺ፪፻፴፮/፪ሺ፲፫

የፌዴራል የስነ-ምግባርና የፀረ ሙስና ኮሚሽን ማቋቋሚያ አዋጅ..............................ገጽ ፲፪ሺ፱፻፹፬


**Content**


Proclamation No. 1236/2021

Revised Federal Ethics and Anti-Corruption Commission Proclamation............Page 12984


### አዋጅ ቁጥር ፩ሺ፪፻፴፮ /፪ሺ፲፫

### የፌዴራል የስነ-ምግባርና የፀረ ሙስና ኮሚሽን ማቋቋሚያ አዋጅ እንደገና ለማሻሻል የወጣ አዋጅ

የኢትዮጵያ መንግስትና ህዝብ ሙስና እና ብልሹ አሰራር የሀገራችን ማህበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊ እና ፖለቲካዊ እድገት የሚገታ ተግባር መሆኑን በመገንዘብ የህግ ስርዓት መዘርጋት አስፈላጊ በመሆኑ፤

በሀገራችን የተጀመረውን የልማት፣ የሰላም እና የዴሞክራሲያዊ ስርዓት ግንባታ ቀጣይነት ያለው እንዲሆን ሙስና እና ብልሹ አሰራርን መከላከል በመልካም ስነ-ምግባር የተገነባ፣ ሙስናን የሚፀየፍ በፅናት የሚታገል ህብረተሰብ መፍጠር አስፈላጊ በመሆኑ፤

የኮሚሽኑ አሠራር የግልጽነት እና የተጠያቂነት መርሆዎችን የተከተለ እንዲሆን በማድረግ ኮሚሽኑ ተቋማዊ እና የአሰራር ነፃነት እንዲኖረው ማድረግ ተገቢ በመሆኑ፤

### PROCLAMATION No. 1236/2021

### THE REVISED PROCLAMATION FOR THE ESTABLISHMENT OF THE FEDERAL ETHICS AND ANTI-CORRUPTION COMMISSION PROCLAMATION

**WHEREAS**, the Government and the Peoples of Ethiopia recognize that corruption and impropriety are capable of hindering the Social, Economic and Political development of our country and found it necessary to establish a legal system;

**WHEREAS**, it has become necessary to prevent corruption and impropriety and to create a society of good ethical values and moral which shall not condone but rather prepared to resolutely combat corruption; in order to promote and sustain the development, peace and democratic process in our country;

**WHEREAS**, it has become proper for the commission to have independence and impartiality in its operation by making its operation and activities be guided with the principles of transparency and accountability;

ለኮሚሽኑ በተለያዩ አዋጆች የተሰጡትን ስልጣንና ተግባራት በአንድ ላይ ማሰባሰብ አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ እና ኮሚሽኑ በሀገር ደረጃ የፀረ ሙስና ትግሉን የመምራት እና የማስተባበር ሚናውን ለመወጣት የሚያስፈልገውን የኃላፊነት ወሰን በህግ መደንገግ በማስፈለጉ፣

የሙስና መከላከል ተግባር በአንድ ተቋም ተጀምሮ የሚጠናቀቅ ባለመሆኑ ኮሚሽኑ ከሌሎች ተቋማት ጋር የሚኖረው ግንኙነት የህግ ድጋፍ እንዲኖረው በማድረግ ከፀረ ሙስና ትግል አኳያ በአለም አቀፍ እና በአህጉር ደረጃ ሀገሪቱን በብቃት እንዲወክል ማድረግ አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ፣

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ህገ መንግስት አንቀፅ ፶፭ ንዑስ አንቀጽ (፩) መሰረት የሚከተለው አዋጅ ታውጇል፡፡

## ክፍል አንድ
## ጠቅላላ

### ፩. አጭር ርዕስ

ይህ አዋጅ "የፌዴራል የስነ-ምግባርና የፀረ ሙስና ኮሚሽን ማቋቋሚያ አዋጅን ለማሻሻል የወጣ አዋጅ ቁጥር ፩ሺ፪፻፴፮/፪ሺ፲፫" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

### ፪. ትርጓሜ

የቃሉ አግባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ አዋጅ ውስጥ፦

፩/ "ኮሚሽን" ማለት የፌዴራል የሥነ-ምግባርና የፀረ ሙስና ኮሚሽን ነው፣

፪/ "ኮሚሽነር ወይም ምክትል ኮሚሽነር" ማለት እንደ ቅደም ተከተሉ የኮሚሽኑ ኮሚሽነር ወይም ምክትል ኮሚሽነር ነው፣

**WHEREAS**, it has become necessary to consolidate in one the powers and duties given to the Commission by different laws and provide in law the scope of power of the commission that would enable it accomplish its role of leading and coordinating the anticorruption struggle at the national level;

**WHEREAS**, corruption prevention is not a task that begins and ends in a given institution and it has become necessary to provide in law the relations of the Commission would have with other institutions so as to make the Commission adequately represent the nation at international and continental level in the area of anticorruption struggle ;

**NOW, THEREFORE**, in accordance with Article 55(1) of The Constitution of the Federal Democratic Republic of Ethiopia, it is hereby proclaimed as follows.

## PART ONE
## GENERAL

### 1. Short Title

This Proclamation may be cited as the "Revised Federal Ethics and Anti-Corruption Commission Proclamation No. 1236/2021"

### 2. Definition

Unless the context requires otherwise in this Proclamation:

1/ "Commission" means The Federal Ethics and Anti-Corruption Commission;

2/ "Commissioner or Deputy commissioner" means the Commissioner or the DeputyCommissioner of the Commission respectively;

፫/ "የመንግስት መስሪያ ቤት" ማለት ሙሉ በሙሉ ወይም በከፊል በመንግስት በጀት የሚተዳደር እና የፌዴራል መንግስቱ ስራዎች የሚከናወኑበት ማናቸውም መስሪያ ቤት ነው፣

፬/ "የመንግስት የልማት ድርጅት" ማለት የመንግስት ባለቤትነት ድርሻ በሙሉ ወይም በከፊል ያለበት ማንኛውም የፌዴራል መንግስት የልማት ድርጅት ወይም የአክሲዮን ኩባንያ ነው፣

፭/ "ህዝባዊ ድርጅት" ማለት በማንኛውም አግባብ ከአባላት ወይም ከህዝብ የተሰበሰበ ወይም ለህዝባዊ አገልግሎት ታስቦ የተሰበሰበ ገንዘብ፣ ንብረት ወይም ሌላ ሃብትን የሚያስተዳደር አካልንና አግባብነት ያለው ኩባንያን የሚያካትት የግል ዘርፍ ሲሆን የሚከተሉትን አያካትትም፡-

ሀ) የሃይማኖት ድርጅትን፣

ለ) የፖለቲካ ድርጅትን(ፓርቲን)፣

ሐ) የዓለም አቀፍ ድርጅትን፣ እና

መ)ዕድርንና ተመሳሳይ ባህላዊ ወይም ሃይማኖታዊ ይዘት ያለው ማህበርን፡፡

፮/ "የመንግስት ባለስልጣን" ማለት ለዚህ አዋጅ አፈጻጸም ሲባል የህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት አባላት፣ አፈጉባኤና ምክትል አፈጉባኤ፣ የፌዴሬሽን ምክር ቤት አፈጉባኤና ምክትል አፈጉባኤ፣ የሪፐብሊኩን ፕሬዚዳንት፣ ጠቅላይ ሚኒስቴርና ምክትል ጠቅላይ ሚኒስቴር፣ ሚኒስቴሮች፣ ሚኒስቴርዴኤታዎች፣ ኮሚሽነሮች፣ ምክትል ኮሚሽነሮች፣ ዳይሬክተሮች፣ ምክትል ዳይሬክተሮች፣ ስራአስኪያጆች፣ ምክትል ስራ አስኪያጆች፣ የፌዴራል ፍርድ ቤቶች ፕሬዚዳንት፣ ምክትል ፕሬዚዳንት እና ዳኞች፣ ዋና ጠቅላይ አቃቤ ህግ፣ ምክትል ጠቅላይ አቃቤ ህግ እና አቃቢያን ህጎች፣ የዩኒቨርስቲ

3/ "Public Office" means any office the budget of which is fully or partially allocated by the Government and in which any Federal Government activity is performed;

4/ "Public Enterprise" means any Public Enterprise or Share Company the ownership of which is fully or partly owned by the Federal Government;

5/ "Public Organization" means a body that administers money, property or other resources collected in any form from members or the public or collected for public service and includes the private sector company or organization; it may not however include the following:

a) Religious organization;
b) Political organization/parties;
c) International organizations; and
d) Edir or other traditional or religious association;

6/ "Public Official" for the purpose of this Proclamation, means Members, Speakers and Deputy Speakers of the House of People's Representatives, Speakers and Deputy Speakers of the House of the Federation, the President of the Republic, the Prime Minister, Deputy Prime Minister, Ministers, State Ministers, Commissioners, Vice Commissioners, Directors, Deputy Directors, General Managers, Deputy General Managers , Presidents, Vice Presidents and Judges of Federal Courts, the Attorney General, Deputy Attorney

ፕሬዚዳንቶችና ምክትል ፕሬዚዳንቶች፣ የኮሌጅ ዲኖችንና ምክትል ዲኖች፣ የሆስፒታል ስራ አኪያጆች እና ሌሎች በተመሳሳይ በሁሉም ደረጃ የሚገኙትን የስራ ኃፊዎችን ያካትታል፤

፯/ "የመንግስት ሰራተኛ" ማለት በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ ፮ ውስጥ ከተጠቀሱት ውጭ በማንኛውም የመንግስት መስሪያ ቤት ውስጥ ተቀጥሮ ወይም ተመድቦ በቋሚነት ወይም በጊዜዊነት ከ፫ ወር በላይ ለተራዘመ ጊዜ የሚሰራ ሰው ነው፤

፰/ "የመንግስት የልማት ድርጅት ባለስልጣን" ማለት ለዚህ አዋጅ አፈፃፀም ሲባል የድርጅቱ የዳይሬክተሮችና የስራ አመራር ቦርድ ሰብሳቢና አባላትን፣ የድርጅቱ ኃላፊ እና ምክትል ኃላፊዎችን፣ በቦርዱ ወይም በስራ አመራሩ ወይም በሌላ ስልጣን በአለው አካል የተሾመ ወይም የተመደበ የስራ ኃላፊን ያካትታል፤

፱/ "የህዝባዊ ድርጅት ባለስልጣን" ማለት ለዚህ አዋጅ አፈፃፀም ሲባል የድርጅቱ የዳይሬክተሮችና የስራ አመራር ቦርድ ሰብሳቢና አባላትን፣ የድርጅቱ ኃላፊ እና ምክትል ኃላፊዎችን፣ በቦርዱ ወይም በድርጅቱ የበላይ ኃላፊ ወይም በሌላ ስልጣን በአለው አካል የተሾመ ወይም የተመደበ የስራ ኃላፊን ያካትታል፤

፲/ "የመንግስት የልማት ድርጅት ወይም የህዝባዊ ድርጅት ሰራተኛ" ማለት በድርጅቱ ውስጥ ተቀጥሮ ወይም ተመድቦ በቋሚነት ወይም በጊዜዊነት ከ፫ወር በላይ ለተራዘመ ጊዜ የሚሰራ ሰው ነው፤

General and Public Prosecutors, Presidents and Deputy Presidents of Universities; Deans and Deputy Deans of Colleges; Directors of Hospitals and other officials with similar rank at all levels;

7/ "Public Employee" means any person, other than those referred to under Sub-Article (6) of this Article, employed or assigned, and working in any public office permanently or temporarily for a period of time longer than three months;

8/ "Official of a Public Enterprise" for the purpose of this proclamation shall include Chairman and Members of the Board of directors or Boards of Management of the Enterprise, the Head and Deputy Heads of the enterprise as well as any management member appointed or assigned by the Board, Board of Management or any other competent body;

9/ "Official of a Public Organization" for the purpose of this proclamation shall include Chairman and Members of the Board of Directors or Board of Management of the organization, the Head and Deputy Heads of the organization as well as any management member appointed or assigned by the Board, head of the Organization or any other competent body;

10/ "Employee of a public enterprise or public organization" means any person employed or assigned and working in any public enterprise or organization permanently or temporarily for a period of time longer than three months;

፲፩/ "የስነምግባር መከታተያ ክፍሎች" ማለት በመንግስት መስሪያ ቤት ወይም በመንግስት ልማት ድርጅቶች ወይም በህዝባዊ ድርጅቶች ውስጥ የስነምግባርና የፀረ ሙስና ኮሚሽን ስራውን በየተቋማቱ ለማስራት የሚያደራጃቸው አደረጃጀቶች ናቸው፣

፲፪/ "የስነምግባር መከታተያ ክፍል ኃላፊ ወይም ሰራተኛ" ማለት በመንግስት መስሪያ ቤት ወይም በመንግስት ልማት ድርጅት ወይም በህዝባዊ ድርጅት ውስጥ ተመድቦ ወይም ተቀጥሮ የሚሰራ ማለት ነው፣

፲፫/ "አደረጃጀቶች" ማለት ኮሚሽኑ በመንግስት ወይም በግል የትምህርት ተቋማት ዉስጥ መልካም ስነምግባርን ለመገንባት እና ሙስናን ለመከላከል እንዲያስችለው የሚያደራጃቸው የተማሪዎች የስነ-ምግባርና የፀረ ሙስና ክበባት ወይም በመንግስት መስሪያ ቤት፣ የመንግስት ልማት ድርጅት እና ህዝባዊ ድርጅት ውስጥ የሚፈጠሩ ሌሎች ልዩ ልዩ አደረጃጀቶች ናቸው፣

፲፬/ "ለህዝባዊ አገልግሎት የተሰበሰበ ሃብት" ማለት የተወሰነ የህብረተሰብ ክፍልን ወይም ህብረተሰቡን በአጠቃላይ ለመርዳት ወይም ለመደገፍ ወይም ለማበረታታት ወይም ለማልማት ታስቦ የተሰበሰበ ወይም ለዚሁ ዓላማ እንዲውል በማንኛውም መንገድ የተገኘ እና በበጎ አድራጎት ድርጅት ወይም ማህበር ወይም ይህን ዓላማ ለማሳካት ተብሎ በተደራጀ ወይም በተቋቋመ ኮሚቴ የሚተዳደር ወይም የሚንቀሳቀስ ገንዘብ፣ ንብረት ወይም ሃብት ነው፣

11/ "Ethics Liaison Units" are organizations that the ethics and anticorruption commission creates under public offices, public enterprises or public organizations for it to accomplish its tasks in the respective institutions;

12/ "Ethics officer or employee of ethics liaison unit" means any person assigned or employed and working in public offices, public enterprises or public organizations;

13/ "Mass Organizations" means students' ethics and anticorruption clubs the commission creates in public or private educational institutions, or other various organizations created in public offices, public enterprises and public organizations so as to enable it to enhance good ethical values and prevent corruption;

14/ "Resource collected for public purpose" means money, property or resource that is collected with the intent to support, assist, encourage or develop the whole or a section of the community or obtained in any way with such intent and administered or utilized by a charity or association or a committee organized or formed for such purpose;

፲፭/ "የባንክ ሂሳብ" ማለት በባንክ የተቀመጠ ገንዘብ፣ ወርቅ እና የመሳሰሉት ውድ እቃዎች እንዲሁም አንድ ደንበኛ ከባንኩ ጋር የሚያደርጋቸውን ማናቸውንም ግንኙነቶች /ትራንዛክሽኖች/ የሚያጠቃልል ነው፣

፲፮. "ጠቋሚ" ማለት ሊፈፀም ነው ብሎ ያመነውን የሙስና ወንጀል ወይም የሃብት ምዝገባ ትክክለኛ አለመሆንን የሚመለከት መረጃ ለኮሚሽኑ ወይም ለስነ-ምግባር መከታተያ ክፍሎች የሚያቀርብ ማንኛውም ሰው ነው፤

፲፯/ "ሀገራዊ የፀረ ሙስና ፖሊሲ እና ስትራቴጂ" ማለት መልካም ስነምግባርን በመገንባት፣ ሙስናን በመከላከል እና በመዋጋት ረገድ በአጭር እና በረጅም ጊዜ ሀገሪቱ ልትደርስበትየምታስበውን ደረጃ የሚያመላክት ሀገራዊ ሰነድ ነው፣

፲፰/ "ሰው" ማለት የተፈጥሮ ሰው ወይም በህግ የሰውነት መብት የተሰጠው አካል ነው፤

፲፱/ በወንድ ፆታ የተገለጸዉ ሴትንም ይጨምራል፡

15/ "Bank Account" means money, gold and other similar precious items deposited in a bank and includes any transaction a customer has with a bank;

16/ "Whistle blower" means any person who reports to the commission or ethics liaison units a corruption offense intended to be committed or inaccurate asset registration;

17/ "National Anticorruption Policy and Strategy" means a national document that indicates the level the country envisages of achieving in the short and long term in building good ethical conduct, preventing and combating corruption;

18/ "Person" means natural or juridical person;

19/ Any expression in the masculine gender includes the feminine.

## ክፍል ሁለት
## ስለኮሚሽኑ መቋቋም፣ ስልጣንና ተግባር

### ፫. የኮሚሽኑ መቋቋም

፩/ የፌዴራል የሥነ-ምግባርና የፀረ ሙስና ኮሚሽን ከዚህ በኋላ ኮሚሽን እየተባለ የሚጠራ የፌዴራል መንግስት መስሪያ ቤት ሆኖ በአዋጅ ተቋቁሟል፣

፪/ ኮሚሽኑ ተጠሪነቱ ለህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ይሆናል፣

፫/ የአዲስ አበባ እና የድሬደዋ ከተማ አስተዳደሮች የራሳቸውን ኮሚሽን ያቋቁማሉ፡፡

## PART TWO
## ESTABLISHMENT AND POWERS AND DUTIES OF THE COMMISSION

### 3. Establishment of the Commission

1/ The Federal Ethics and Anti-Corruption Commission (hereinafter referred to as "the Commission") is hereby established as the Federal Government office.

2/ The Commission shall be accountable to the House of Peoples Representatives.

3/ The Addis Ababa and Dire Dawa City Administrations shall establish their own ethics and Anticorruption commission.

## ፬. ስለ ኮሚሽኑ የአሰራር ነፃነት

ኮሚሽኑ ሙስና ለመከላከል በሚያደርገው እንቅስቃሴ ከማንኛውም ሰው ወይም አካል ጣልቃ ገብነት ነፃ ነው፡፡

## ፭. ዋና መስሪያ ቤት

የኮሚሽኑ ዋና መስሪያ ቤት አዲስ አበባ ይሆናል፤

## ፮. የኮሚሽኑ ዓላማዎች

ኮሚሽኑ የሚከተሉት ዓላማዎች ይኖሩታል፡-

፩/ የትውልድ ስነምግባር እና የሞራል እሴቶችን በብቃት መገንባት፤

፪/ የሙስና ወንጀልን እና ብልሹ አሰራርን መከላከል፤

፫/ ለፀረ ሙስና ትግሉ አጋዥ የሆነ የህዝብ ንቅናቄ በመፍጠር ህዝቡ የፀረ ሙስና ትግሉ ባለቤት እንዲሆን ማስቻል፤

፬/ በህግ የተሰጡትን ስልጣን እና ተግባር ለመፈጸም የሚያስችል ተቋማዊ አቅም መገንባት፤

፭/ በመንግስት መ/ቤቶች፣ በመንግስት የልማት ድርጅቶች እና በህዝባዊ ድርጅቶች ውስጥ የሚገኙ የህዝብ ተመራጮች፣ የመንግስት ተሿሚዎች፣ የመንግስት ሰራተኞች የመንግስት ልማት ድርጅቶችና የህዝባዊ ድርጅቶች የስራ ኃላፊዎች እና ሰራተኞች ሃብት እና የገቢ ምንጮቻቸውን በማሳወቅ፣ በመመዝገብ፣ ተደራሽ በማድረግ፣ ትክክለኛነቱን በማረጋገጥ የግልፅነት እና የተጠያቂነትን ስርዓት መፍጠር ነው፡፡

## 4. Independence of the Commission

The Commission shall be free from any interference from any person or organ with regard to activities undertaken to prevent corruption.

## 5. Head Office

The Commission shall have its Head Office in Addis Ababa.

## 6. Objectives of the Commission

The Commission shall have the following objectives to:

1/ Effectively enhance ethical and moral values of the generation;

2/ Prevent corruption offences and other improprieties;

3/ Make the public become owner of the anti-corruption struggle by creating a popular movement helpful in the fight against corruption;

4/ Create institutional capacity that would enable to carry out powers and duties given to it by law;

5/ Ensure transparency and accountability in public offices, public enterprises and public organizations by having the asset and financial interests of their officials and employees declared, registered and made accessible and verified as to its accuracy;

## ፯. የኮሚሽኑ ስልጣንና ተግባር

ኮሚሽኑ የሚከተሉት ስልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፡-

፩/ ሀገራዊ የፀረ ሙስና ፖሊሲ እና ስትራቴጂ ያዘጋጃል፣ያስፀድቃል፣አፈፃጸሙን ይከታተላል፣

፪/ በመንግስት መስሪያ ቤቶች፣ በመንግስት የልማት ድርጅቶች እና በህዝባዊ ድርጅቶች የሚሾሙ ወይም የሚመደቡ ወይም የሚቀጠሩ የስራ ኃላፊዎች እና ሰራተኞች ስራ ከመጀመራቸው በፊት የስነምግባር እና የሙስና መከላከል ስልጠና እንዲወስዱ ያደርጋል፣

፫/ በመንግስት መስሪያ ቤቶች፣ በመንግስት የልማት ድርጅቶች እና በህዝባዊ ድርጅቶች ውስጥ ለሙስናና ብልሹ አሰራር የተጋለጡ እና ሊጋለጡ የሚችሉ የአሰራር ስርዓቶችን በማጥናት ወይም እንዲጠኑ በማድረግ የተሰጡ የመፍትሄ /የማሻሻያ/ ሃሳቦችን ያቀርባል፣ተግባራዊ መሆናቸውን ይከታተላል፣ በማይፈፅሙት ላይ ተገቢ የሆነ እርምጃ እንዲወሰድ በህግ የመመርመርና የመክሰስ ስልጣን ላለዉ አካል ያቀርባል፣

፬/ ኮሚሽኑ ሙስና ለመፈፀም የሚያስችል ዝግጅት እየተደረገ መሆኑን ሲጠረጥር ወይም ጥቆማ ሲደርሰዉ ድርጊቱ ከመፈፀሙ በፊት አስቸኳይ የሙስና መከላከል ስራ በመስራት ሂደቱ እንዲቋረጥ ወይም አስፈላጊውን ማስተካከያ የማድረግ ስልጣን አለው፡፡ ሆኖም ግን በተደረገው ክትትል ሙስና ስለመፈፀሙ ጥርጣሬ ሲኖረው በህግ የመመርመርና የመክሰስ ስልጣን ላለዉ አካል ያቀርባል፣

## 7. Powers and Duties of the Commission

The Commission shall have the following powers and duties to:

1/ Prepare National Anti-Corruption Policy and Strategy; have it approved and follow up its implementation;

2/ Provide or cause the provision of training on ethics and corruption prevention to officials, heads and employees appointed, assigned or employed in public offices, enterprises and organization before engaged to the work;

3/ Study or cause to be studied practices and work procedures in Public Offices, Public Enterprises and public organizations prone or conducive to corruption and improprieties in order to give recommendations and follow up their implementation, report for an organ which has the power to investigate and prosecute to take the proper measures on those failing to implement;

4/ Where the Commission suspects or receive information a preparation for the commission of corruption is underway, by undertaking a rapid corruption prevention activity, suspend the operation or cause the taking of the necessary correction. Where it has, however, suspicion about the commission of corruption in the process it shall report same to the relevant organ which has the power to investigate and prosecute ;

፭/ የህዝብ ተመራጮችን፣የመንግስት ተሿሚዎችን እና የመንግስት ሰራተኞችን፣ የመንግስት የልማት ድርጅቶች እና የህዝባዊ ድርጅቶች የስራ ኃላፊዎችና ሰራተኞች ሃብታቸውን እንዲያሳውቁ፣ እንዲያስመዘግቡ፣ ትክክለኛነቱ እንዲረጋገጥ፣ መረጃው በአግባቡ ተደራጅቶ እንዲያዝና ተደራሽ እንዲሆን ያደርጋል፣

፮/ የሃብት ምዝገባ፣ ትክክለኛነትን ለማረጋገጥ እና ተደራሽ ለማድረግ የሚያስችል ሶፍት ዌር ያለበለፅጋል፣ ጥቅም ላይ ያውላል፣ ያስተዳድራል:: አግባብነት ያላቸዉ አካላት መረጃ ሲጠይቁ ይህንኑ ከዳታ ቤዝ የተገኘውን መረጃ ይሰጣል፣

፯/ የህዝብ ተመራጮች፣ የመንግስት ተሿሚዎች፣ የመንግስት ሰራተኞች የመንግስት የልማት ድርጅቶች እና የህዝባዊ ድርጅቶች የስራ ኃላፊዎች እና ሰራተኞች ከተሰጣቸው ኃላፊነት፣ ከመቆጣጠር እና ከመወሰን ስልጣን ጋር በተያያዘ የሚፈጠር የጥቅም ግጭትን ለመከላከል የሚያስችል ስርዓት ይዘረጋል፣ አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ ተገቢ የሆነ እርምጃ እንዲወሰድ በህግ የመመርመርና የመክሰስ ስልጣን ላለዉ አካል ያቀርባል፡፡ ዝርዝሩ በደንብ ይወሰናል፣

፰/ ሙስናን በመታገል እና በመከላከል ረገድ ጥሩ ውጤት ያስገኙ መስሪያ ቤቶችን፣ ድርጅቶችን ግለሰቦችን፣ እና ክበባትን አወዳድሮ እውቅና የሚያገኙበትን እና ለሽልማት የሚበቁበትን ሥርዓትና መለኪያ ይዘረጋል፣ ተግባራዊ ያደርጋል፣

5/ Cause the declaration and registration of the assets and financial interests of elected public officials, public appointees and employees of public offices, heads and employees of public enterprises and public organizations; verify its accuracy, organize such data and make it accessible;

6/ Develop, put to use, and administer software database that would enable an effective asset and financial interest declaration, registration and access. It shall provide information from the database to relevant organs upon request;

7/ Create a system to Prevent conflict of interest of elected officials, public appointees and employees, heads and employees of public enterprises and organizations that would arise in connection with their mandate as well as power of control and decision, and report for an organ which has the power to investigate and prosecute in order for them to take appropriate measure where necessary. Particulars shall be prescribed by regulations;

8/ Establish and implement upon approval procedures and system for the recognition and selection for awards, upon competition, of offices, and organizations, individuals and clubs who are successful in the fight against and prevention of corruption;

፱/ ለህዝብ ተመራጮች፣ ለመንግስት ተሿሚዎች፣ ለመንግስት ሰራተኞች፣ ለመንግስትና ለህዝባዊ ድርጅት የሥራ ኃፊዎች እና ሰራተኞች የሚያገለግል የስነምግባር ደንብ ያዘጋጃል ወይም እንዲዘጋጅ ያደርጋል፣ ያስፀድቃል፣ አፈፃጸሙን ይከታተላል፣

፲/ በመንግስት መስሪያ ቤቶች፣ በመንግስት የልማት ድርጅቶች እና በህዝባዊ ድርጅቶች ውስጥ የሙስና እና ብልሹ አሠራር ተጋላጭነትን ጥናት ያካሂዳል፣ እንደአስፈላጊነቱ ለህዝብ ይፋ ያደርጋል፣

፲፩/ የስነ-ምግባር ግንባታ እና የሙስና መከላከል ተግባራትን ለመፈጸም የሚያስችሉ አደረጃጀቶችን በመንግስት መስሪያ ቤቶች፣ በመንግስት የልማት ድርጅቶች እና በህዝባዊ ድርጅቶች እና በየደረጃው በሚገኙ የትምህርት ተቋማት ያደራጃል፣

፲፪/ የፀረ ሙስና ህጎች መከበራቸውን ይከታተላል፣ ያረጋግጣል፣ ስለአፈፃጸማቸው የምክር አገልግሎት ይሰጣል፣

፲፫/ በመንግስት መስሪያ ቤቶች፣ በመንግስት የልማት ድርጅቶች እና በህዝባዊ ድርጅቶች ውስጥየስነምግባርመከታተያ ዳይሬክቶሬቶችን ወይም ቡድኖችን ወይም ባለሙያዎችን ያደራጃል፣ ይመድባል፣ ያሰማራል፣

፲፬/ የክልል የስነ-ምግባርና የፀረ ሙስና ኮሚሽኖችን ያስተባብራል፣ አስፈላጊውን የቴክኒክ ድጋፍ ያደርጋል፣

፲፭/ ተመሳሳይ ዓላማ ካላቸው ሀገራዊ፣ አህጉራዊ እና ዓለም አቀፋዊ አካላት ጋር ሀገሪቱን በመወከል ግንኙነት እና ትብብር ያደርጋል፣

9/ Prepare, cause to prepare submit for approval and monitor the implementation of Codes of Conduct for elected public officials, public appointees and Public Office employees as well as heads and employees of public enterprises and organizations;

10/ Conduct a study on corruption and impropriety vulnerability in public offices, public enterprises and public organizations; and publicize same if deemed necessary;

11/ Organize mass organizations that would help in the enhancement of ethics and prevention of corruption in public offices, enterprises and organizations and educational institutions at all levels;

12/ Follow up and ensure the respect of anticorruption laws and give a consultancy service on their implementation;

13/ Organize, assign and deploy Ethics Liaison Directorates or Teams or Experts in public offices, public enterprises and public organizations;

14/ Coordinate Regional ethics and anticorruption commissions; and provide them with the necessary technical support;

15/ By representing the country liaise and cooperate with National, Continental and International bodies with similar objectives;

፲፮/ በሀገሪቱ ህግ እና ፖሊሲ መሰረት ዓለም አቀፍ እና አህጉራዊ የፀረ ሙስና ኮንቬንሽኖችን እና ትብብሮች ስራ ላይ እንዲውሉ ያደርጋል፣

፲፯/ ዓለም አቀፋዊ እና አህጉራዊ የፀረ ሙስና ኮንቬንሽኖችን አፈፃፀም በተመለከተ ሀገሪቱን ይወክላል፣

፲፰/ የስነ-ምግባር ትምህርትን ለማስፋፋት እና መልካም ስነ-ምግባርን ለመገንባት እንዲያስችለው የራሱ ሚዲያ እንዲቋቋም ይደረጋል፣

፲፱/ በስነ-ምግባር ግንባታ፣ በሙስና ወንጀል ምርመራ እና ክስ የመመስረት ስልጣን ከተሰጣቸዉ እና ከሌሎች አግባብነት ካላቸዉ አካላት የስራ አፈጻጸም ሪፖርት ይቀበላል፣

፳/ የንብረት ባለቤት ይሆናል፣ ውል ይዋዋላል፣ በራሱ ስም ይከሳል እና ይከሰሳል፣

፳፩/ በህግ የሚሰጡትን እና ዓላማውን ከግብ ለማድረስ የሚረዱ ሌሎች ተግባራትን ያከናውናል።

፰. <u>የኮሚሽኑ አቋም</u>

፩/ ኮሚሽኑ በጠቅላይ ሚኒስቴሩ አቅራቢነት በህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት የሚሾሙ ኮሚሽነርና ምክትል ኮሚሽነሮች፣ እና

፪/ ለስራው አስፈላጊ የሆኑ ሰራተኞች

ይኖሩታል።

16/ In accordance with the country's laws and policies cause the implementation of International and Continental anti-corruption conventions and co-operations;

17/ Represent the country with regards to the implementation of International and Continental Anticorruption Conventions;

18/ Cause the establishment of its own independent media to promote ethical education and to enhance good ethical values ;

19/ Receive performance reports from organs mandated with the power of enhancing ethics, the investigation and prosecution of corruption offences and other relevant organs;

20/ Own property, enter into contract, sue and be sued in its own name;

21/ Perform such other duties as may be defined by law and undertake other activities necessary for the attainment of its objectives.

8. <u>Organization of the Commission</u>

The commission shall have;

1/ A Commissioner and Deputy Commissioners to be appointed by the house of peoples' representatives upon nomination by the Prime Minister; and

2/ The necessary staff.

## ፱. የኮሚሽነሩ ስልጣንና ተግባር

፩/ ኮሚሽነሩ የኮሚሽኑ የበላይ ሃላፊ በመሆን የኮሚሽኑን ሥራዎች ያደራጃል፣ ይመራል፣ ያስተዳድራል፡፡

፪/ የዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀጽ (፩) የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ ኮሚሽነሩ፦

ሀ) በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፯ የተዘረዘሩትን የኮሚሽኑን ሥልጣንና ተግባራት በሥራ ላይ ያውላል፣

ለ) የኮሚሽኑን መዋቅር፣ የደመወዝ ስኬል እና ጥቅማጥቅሞቻቸውን በማዘጋጀት ለህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት አቅርቦ በማፀደቅ ከፍያ ይፈፅማል፣ ዝርዝር አፈጻጸሙ በተመለከተ ምክር ቤቱ በሚያወጣው ደንብ መሰረት ይወሰናል፣

ሐ) በዚህ አዋጅ የተመለከቱትን ድንጋጌዎች እና የፌዴራል የመንግስት ሰራተኞች አዋጅ አጠቃላይ መርሆዎችን ጠብቆ ደንብ አዘጋጅቶ ለህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ያቀርባል፣ ሲፀድቅም ተግባራዊ ያደርጋል፣

መ) ለስራው አስፈላጊ የሆኑ ሰራተኞችን ይሾማል፣ ይመድባል፣ ይቀጥራል፣ ያስተዳደራል፣ ያሰናብታል፡፡ ዝርዝር አፈፃፀሙ በሚወጣዉ ደንብ ይወሰናል፣

ሠ) የኮሚሽኑን አመታዊ የሥራ ፕሮግራም እና በጀት አዘጋጅቶ ለምክር ቤቱ ያቀርባል፣ሲፈቀድም በሥራ ላይ ያውላል፣

## 9. Powers and Duties of the Commissioner

1/ The Commissioner shall be the top official of the Commission and, as such, shall organize, direct and manage the activities of the Commission.

2/ Without prejudice to the provisions of Sub-Article (1) of this Article, the Commissioner shall have powers and duties to:

a) Exercise the powers and duties of the Commission specified under Article 7 of this Proclamation;

b) Prepare and submit to the House of Peoples Representative for approval the organizational structure , salary scale and benefit schemes of the employees of the Commission and implement same upon approval; particulars shall be specified in Regulations to be issued by the House;

c) Prepare regulations in line with provisions specified in this Proclamation and the basic principles of Federal public servants Proclamation and submit to the House of Peoples Representatives and implement same upon approval;

d) To appoint, assign, employ, administer and dismiss the necessary staffs. Particulars shall be specified in regulations to be issued;

e) Prepare the annual work program and budget of the Commission and submit to the House and implement same upon approval;

ረ) ለኮሚሽኑ በተፈቀደለት በጀት እና በአዘጋጀው የሥራ ፕሮግራም መሠረት የፋይናንስ ሕግን ተከትሎ ገንዘብ ወጪ ያደርጋል፣

ሰ) ኮሚሽኑ ከሶስተኛ ወገኖች ጋር በሚያደርጋቸው ግንኙነቶች ኮሚሽኑን ይወክላል፣

ሸ) የኮሚሽኑን ጠቅላላ የሥራ አፈጻጸምና የሂሳብ ሪፖርት አዘጋጅቶ ለምክር ቤቱ ያቀርባል፣

ቀ) በሃብት ምዝገባ፣ ትክክለኛነት ማረጋገጥ እና የጥቅም ግጭትን በማስተዳደር ሂደት አስፈላጊ በሆነ ጊዜ የማንኛውም ሰው ወይም ድርጅት የባንክ ሂሳብ እንዲፈተሽ እና አስፈላጊው መረጃ እንዲሰበሰብ ትዕዛዝ መስጠት ይችላል፣

በ) በሃብት ምዝገባ ትክክለኛነት፣ በአስቸኳይ ሙስና መከላከል እና በሌሎች የሙስና መከላከል ተግባራት ለኮሚሽኑ ጥቆማ በመስጠታቸዉ ምክንያት የቂም በቀል እርምጃ ሊደርስባቸዉ የሚችሉ ጠቋሚዎች ሲኖሩ ተገቢዉን ማጣራት በማድረግ በህግ መሰረት ከለላ እና ጥበቃ እንዲደረግላቸዉ በህግ ስልጣን ለተሰጠዉ አካል ያስተላልፋል፡፡

፫/ ኮሚሽነሩ ለኮሚሽኑ ሥራ ቅልጥፍና በሚያስፈልግ መጠን ሥልጣንና ተግባሩን በከፊል ለኮሚሽኑ የስራ ኃላፊዎች እና ሠራተኞች በውክልና ሊያስተላልፍ ይችላል፡፡

## ፲. የምክትል ኮሚሽነሩ ስልጣን እና ተግባር

፩/ ምክትል ኮሚሽነሩ፡-

ሀ) የኮሚሽኑን ተግባሮች በማቀድ፣ በማደራጀት፣ በመምራትና በማስተባበር ኮሚሽነሩን ይረዳል፣

f) Effect expenditure in accordance with approved budget and work program of the Commission as per relevant financial laws;

g) Represent the Commission in its dealings with third parties;

h) Submit general performance and financial reports of the Commission to the House;

i) Where necessary, to give order for the search of bank accounts of any person or organization and gathering of the necessary information in the process of asset registration, registration verification and management of conflict of interest;

j) Report for organs which has given by law to safeguard informants if there is threat on persons who give information to the Commission with regard to asset registration verification, immediate corruption prevention and others corruption prevention activities;

3/ The Commissioner may delegate part of his powers and duties to the officials and employees of the Commission to the extent necessary for the effectiveness and efficiency of the Commission.

## 10. Powers and Duties of the Deputy Commissioner

1/ The Deputy Commissioner, shall:

a) Assist the Commissioner in planning, organizing, directing and coordinating the functions of the Commission;

ለ) በኮሚሽኑ መዋቅር መሠረት የሥራ ክፍፍል በማድረግ ከኮሚሽኑ ዘርፎች ከፊሉን ይከታተላል፣

ሐ) ኮሚሽነሩ በማይኖርበት ጊዜ እሱን ተክቶ ይሰራል፣

መ) ከኮሚሽነሩ ተለይተው የሚሰጡትን ሌሎች ተግባሮች ያከናውናል፣

፪/ ምክትል ኮሚሽነሩ ተጠሪነቱ ለኮሚሽነሩ ይሆናል፣

፫/ ኮሚሽነሩ በማይኖርበት ጊዜ በኮሚሽነሩ በሌላ ሁኔታ ካልተወሰነ በስተቀር የሹመት ቅድሚያ ያለው ምክትል ኮሚሽነር ኮሚሽነሩን ተክቶ ይሰራል፡፡ ሆኖም ግን ምክትል ኮሚሽነሮቹ በተመሳሳይ ጊዜ የተሾሙ ከሆኑ ከምክትል ኮሚሽነሮቹ መካከል ኮሚሽነሩ አንዱን ሊወክል ይችላል፡፡

፲፩. የኮሚሽነሩ እና የምክትል ኮሚሽነሩ የስራ ዘመንና ከስራ ስለመነሳት

፩/ የኮሚሽነሩ እና የምክትል ኮሚሽነሩ የሥራ ዘመን ለስድስት ዓመት ይሆናል፣ ሆኖም ግን አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ እንደገና ለአንድ የስራ ዘመን ብቻ ሊሾም ይችላል፣

፪/ ኮሚሽነሩ ወይም ምክትል ኮሚሽነሩ ከዚህ በታች በተመለከቱት ሁኔታዎች ካልሆነ በስተቀር የተሾመበት የሥራ ዘመን ከማለቁ በፊት ከፈቃዱ ውጭ ከሥራው አይነሳም:-

ሀ) አግባብነት ባለው የሥነ ምግባር ደንብ የተመለከቱትን ድንጋጌዎች ተላልፎ ሲገኝ፣

b) Follow up part of the Commission's departments by sharing functions in accordance with the structure of the Commission;

c) Act on behalf of the Commissioner in the absence of the later;

d) Perform such other duties as may be specifically entrusted to him by the Commissioner;

2/ The Deputy Commissioner shall be accountable to the Commissioner;

3/ Unless specified otherwise the Deputy Commissioner having seniority in appointment shall act on behalf of the Commissioner in the absence of the latter. However, when the Deputy Commissioners are appointed at the same time, the commissioner may assign one of them.

11. **Term of Office and Removal from Office of the Commissioner and the Deputy Commissioners**

1/ The term of office of the Commissioner and the Deputy Commissioner shall be for six years; he may, however, be reappointed for only one term where necessary.

2/ Once appointed, the Commissioner or the Deputy Commissioner may not be removed, except on his own will, from his office unless:

a) He has violated the provisions of the relevant code of conduct;

ለ) ጉልህ የሆነ የሥራ ችሎታና የቅልጥፍና ጉድለትአሳይቷልተብሎ ሲታመን፣

ሐ) በጤና ችግር ምክንያት ተግባሩን በተገቢው ሁኔታ ማከናወን የማይችል ሆኖ ሲገኝ፣

መ) የጡረታ እድሜ ላይ ሲደርስ ይሆናል፣

፫/ በንዑስ አንቀፅ (፪) በፊደል ተራ (ሀ) እና (ለ) ያሉት ድንጋጌዎች ተፈፃሚ የሚሆኑት በህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ተጣርቶ በአብላጫ ድምጽ ሲደገፍ ነዉ፡፡

## ፲፪. ስለኮሚሽኑ ሠራተኞች ቅጥር ሁኔታ

የኮሚሽኑ ሠራተኞች የቅጥር፣ አስተዳደርና ስንብት ሁኔታ በዚህ አዋጅ የተመለከቱትን ድንጋጌዎች እና የፌዴራል ሲቪል ሰርቪስ ህግ አጠቃላይ መርሆዎችን መሠረት በማድረግ ምክር ቤቱ በሚያወጣው ደንብ መሠረት ይሆናል፡፡

## ፲፫. ቃለመሀላ ስለመፈፀም

በኮሚሽኑ የተቀጠረ ማንኛውም ሠራተኛ ለፌደራሉ ህገ መንግስት ታማኝ በመሆን የተጣለበትን ህዝባዊ አደራና ሙያዊ ሀላፊነት ለመወጣት ቃለመሀላ ይፈጽማል፡፡ የቃለመሀላው ዝርዝር ይዘት በደንቡ ይወሰናል፡፡

## ፲፬. የኮሚሽኑ ሠራተኞች መብት

፩/ ማንኛውም የኮሚሽኑ የስራ ሃላፊዎችና ሠራተኞች ደሞዝና ጥቅማጥቅም ከስራቸዉ ልዩ ባህሪ ጋር በተያያዘ የህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት በሚያፀድቀው የደመወዝ ስኬል እና ጥቅማጥቅም ዉሳኔ መሰረት ተግባራዊ ይሆናል፡፡ ዝርዝሩ ይህን አዋጅ ለማስፈፀም በሚወጣ ደንብ የሚወሰን ይሆናል::

b) He has shown manifest incompetence and inefficiency;

c) He can no longer carry out his responsibilities on account of illness;

d) On attaining retirement age.

3/ The provisions in Sub Article (2) (a) and (b) of this Article shall apply where it has been verified by the House and voted on by majority vote.

## 12. Employment of Employees of the Commission

The terms and conditions of Assignment, employment, administration and dismissal of the employees of the Commission shall be in accordance with the regulations to be issued by the House following the provisions laid down in this Proclamation and the general principles of the Federal Civil Service Law.

## 13. Taking of an Oath

Any person shall upon Assigned or employed in the Commission take oath that he will be faithful to the Federal Constitution and fulfill the demands of public trust and professional responsibility bestowed on him. Details regarding the oath shall be specified in the administrative regulation

## 14. Rights of Employees

1/ Any officials and employees of the Commission is entitled to a salary and benefits in accordance with a special salary scale and benefit scheme approved by the House of Peoples Representatives In view of the special nature of their work. Details shall be specified in regulation to be issued as per this proclamation.

፪/ የማንኛውም ሠራተኛ ደመወዝ፦

ሀ) በሠራተኛው ስምምነት፣
ለ) በፍርድ ቤት ትእዛዝ፣
ሐ) በህግ በተደነገገው መሠረት፣
ካልሆነ በስተቀር ሊያዝ ወይም ሊቆረጥ አይችልም፡፡

፫/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፪)(ለ) ወይም(ሐ) መሠረት ከሠራተኛ ደመወዝ በየወሩ የሚቆረጠው ከደመወዙ አንድ ሶስተኛ አይበልጥም::

፬/ ማንኛውም የኮሚሽኑ ቋሚ ሠራተኛ በጡረታ ሕግ መሠረት የጡረታ መብት ይኖረዋል፣

፭/ የኮሚሽኑ ሠራተኛ፦

ሀ) ሥራውን በተገቢው መንገድ በመወጣት ላይ እያለ ለሚደርስበት ተጠያቂነት በኮሚሽኑ ወጪ ድጋፍና የጥብቅና አገልግሎት ያገኛል፡፡ ዝርዝር አፈፃፀሙ በደንብ ይወሰናል፣

ለ) በማንኛውም አጋጣሚ የበላይ ሀላፊዎችን በአግባቡ የመጠየቅ፣ ስህተት ሲያይ የመጠቆም፣ በውይይት ችግሮችን የመፍታት እንዲሁም የስልጣን ተዋረድን ጠብቆ አቤቱታ ማቅረብ ይችላል፣

ሐ) የሰራተኞች ቅሬታንና የዲስፒሊን ጉዳዮችን በተመለከተ በኮሚሽኑ ዉስጥ በኮሚሽኑ ዉሳኔ ቅር የተሰኘ ወይም ያልተስማማ ሰራተኛ ቅሬታዉን አግባብነት ላለዉ አካል የማቅረብ መብት ይኖረዋል፣ ዝርዝር አፈጻጸሙ በሚወጣዉ ደንብ ይወሰናል፣

2/ The salary of any employee may not be attached or deducted except in accordance with,

a) A written consent of the employee;
b) A court order; or
c) Provisions of the law.

3/ The amount deductible in accordance with Sub Article (2) (b) or (c) of this Article may not exceed one third of the salary of the employee.

4/ Any permanent employee of the Commission is entitled to a pension in accordance with the Pension law.

5/ Any employee of the Commission shall:

a) Be provided with attorney service at the expense of the Commission for any liability incurred while executing his duties properly. Particulars shall be determined by the Regulations;

b) Have the right to appropriately question superiors under any circumstances, inform mistakes, resolve problems through discussion as well as lodge complaints following the chains of command;

c) Have the right to appeal for relevant organ with regard to the decision passed by the Commission in relation to any grievances and discipiline issues; Particulars shall be determined by the regulations;

መ) ከሥራው ጋር በተያያዘ ሁኔታ በሚደርስበት ጉዳት ዘላቂ ወይም ሙሉ ወይም ከፊል የመሥራት ችሎታውን ያጣ የኮሚሽኑ ሠራተኛ አግባብ ባለው ህግ መሰረት የጉዳት ካሳ ይከፈለዋል፣ በጡረታ ህግ መሰረት የተሰጠው መብት ይከበርለታል፡፡ ዝርዝር አፈፃፀሙ በሚወጣው ደንብ ይወሰናል፣

ሠ) የኮሚሽኑ የስራ ኃላፊዎች እና ሰራተኞች ከስራቸው ልዩ ባህሪ ጋር በተያየዘ ደመወዝ እና ልዩ ልዩ ጥቅማጥቅሞችን አስጠንቶ በማቅረብ እና በተወካዮች ምክር ቤት በማፀደቅ ተግባራዊ ይደረጋል፣

ረ) በትርፍ ጊዜው ከሥራው ጋር የጥቅም ግጭት በማይፈጥር ሥራ ላይ ለመስራት መሥሪያ ቤቱን በማሳወቅ ለመስራት ይችላል፡፡ ዝርዝሩ ኮሚሽኑ በሚያወጣው መመሪያ ይወሰናል፡፡

## ፲፭. ከግብር ነፃ ስለመሆን

በዚህ አዋጅ በአንቀፅ ፲፬ በንዑስ አንቀፅ (፭)(መ) መሠረት የሚከፈል የጉዳት ካሳ ክፍያ ከግብር ነፃ ይሆናል፡፡ እንዲሁም በእዳ ሊከበር ወይም በማቻቻያነት ሊቀነስ ወይም ባለመብቱ ሊያስተላልፈው አይችልም፡፡

## ፲፮. ሰራተኛን ከሥራ አግዶ ስለማቆየት

፩/ የኮሚሽኑ ሠራተኛ ከሥራ ታግዶ መቆየት ለሥራው አፈፃፀም ጠቃሚ ሆኖ ከተገኘ ሠራተኛውን ከአንድ ወር ለማይበልጥ ጊዜ ከሥራና ደመወዝ አግዶ ለማቆየት ይቻላል፣

d) Be entitled to benefits provided in the relevant pension law for permanent, total, or partial disability sustained in relation to his duties. particulars shall be specified in the Regulations to be issued;

e) In view of the special nature of their work, the Commission shall have the salary and various benefits of officials and employees of the Commission studied and implement it upon approval by the House of Peoples Representatives;

f) After informing the Commission engages in any other activity which may not have a conflict of interest with his duty, during his leisure time. Details shall be specified in directives to be issued by the Commission.

## 15. Exemption from Tax

Any compensation to be made pursuant to Article 14 Sub-Article (5)(d) of this Proclamation shall be exempt from taxation and may not be attached, deducted by way of setoff or assigned by the beneficiary.

## 16. Suspension from Duty

1/ An employee of the Commission may be suspended from duty by withholding his salary for a period not exceeding one month if that course of action is necessary for the smooth execution of the work;

፪/ በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ (፩) የተደነገገው ቢኖርም የኮሚሽኑ ሠራተኛ በወንጀል ወይም በዲሲፕሊን ጥፋት በህግ የተከሰሰ እንደሆነ እና ተመስክሮ ጥፋቱ ከሥራው የሚያስወጣው መሆኑ ሲገመት ለተጨማሪ አንድ ወር ከሥራ ታግዶ ሊቆይ ይችላል፡፡ ዝርዝሩ ይህን አዋጅ ተከትሎ በሚወጣው ደንብ ይወሰናል፡፡

፲፯. <u>ስለይርጋ ጊዜ</u>

፩/ ቀላል የዲሲፕሊን ቅጣት የሚያስከትል ጥፋት የፈፀመ የኮሚሽኑ ሠራተኛ የምርመራውን ጊዜ ሳይጨምር የፈፀመው ጥፋት ከታወቀበት ቀን ጀምሮ እስከ ስድስት ወር እርምጃ ካልተወሰደበትበዲሲፕሊን ተጠያቂ አይሆንም፣

፪/ ከባድ የዲሲፕሊን ቅጣት የሚያስከትል ጥፋት የፈፀመ የኮሚሽኑ ሠራተኛ የፈጸመው ጥፋት ከታወቀበት ቀን ጀምሮ በአንድ አመት ጊዜ ውስጥ በጥፋቱ ካልተከሰሰ በዲሲፕሊን ተጠያቂ አይሆንም፣

፫/ በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀጽ (፩) ወይም (፪) በተመለከተው የጊዜ ገደብ ውስጥ መወሰድ የሚገባውን የዲሲፕሊን እርምጃ ሳይወስድ የቀረው ኃላፊ ተጠያቂ ይሆናል፡፡

፲፰. <u>በጀት</u>

ኮሚሽኑ ለስራ የሚያስፈልገውን በጀት በማዘጋጀት ለተወካዮች ምክር ቤት አቅርቦ ያፀድቃል፡፡

፲፱. <u>የሂሣብ መዛግብት</u>

፩/ ኮሚሽኑ የተሟሉ እና ትክክለኛ የሂሳብ መዛግብት ይይዛል፡፡

2/ Notwithstanding the provisions of Sub Article (1) of this Article an employee shall be suspended for an additional one month if he is formally charged with a criminal or disciplinary offence for which his dismissal is to be expected if it is proved against him. Details shall be specified in regulations to be issued as per this Proclamation.

17. <u>Period of Limitation</u>

1/ Disciplinary measure may not be taken against an employee of the Commission who has committed an offense entailing simple disciplinary penalty unless such measure is taken within six months, excluding the time required for investigation, from the time the breach of discipline is known;

2/ No disciplinary charge shall be brought against an employee who has committed an offense entailing rigorous disciplinary penalty unless such disciplinary charge is brought within a year from the time the commission of the offense is known;

3/ The Official who has failed to take the measures specified under Sub-Articles (1) or (2) of this Article shall be held responsible.

18. <u>Budget</u>

The Commission prepare its budget and submit for approval to the House.

19. <u>Books of Accounts</u>

1/ The Commission shall keep complete and accurate books of accounts;

፪/ የኮሚሽኑ የሂሳብ መዛግብት እና ገንዘብ ነክ ሰነዶች በፌዴራሉ ዋና ኦዲተር በየዓመቱ ይመረመራል፡፡

## ክፍል ሶስት
## የስነ-ምግባርና መከታታያ ክፍሎችን ስለማደራጀት እና ኮሚሽኑ ከክልል የስነ-ምግባርና የፀረ ሙስና ኮሚሽኖች ጋር ስለሚኖረዉ ግንኙነት

### ፳. የስነ-ምግባር መከታታያ የስራ ክፍል ስለማደራጀት

፩/ ኮሚሽኑ በየደረጃው በሚገኙ በመንግሥት መሥሪያ ቤቶች እና በመንግስት የልማት ድርጅቶች ውስጥ የሥነ-ምግባር ተግባራትን እና የሙስና መከላከል ስራን የሚያስተባብር እና የሚፈፅም የሥነ-ምግባር መከታተያ የስራ ክፍል ያደራጃል፣

፪/ ኮሚሽኑ በየደረጃው በሚገኙ ህዝባዊ ድርጅቶች ውስጥ የሥነ-ምግባር ተግባራትን እና የሙስና መከላከል ስራን የሚያስተባብር እና የሚፈፅም የሥነ-ምግባር መከታተያ የስራ ክፍል እንዲደራጅ ያደርጋል፣

፫/ የሥነ-ምግባር መከታተያ ክፍል ተጠሪነቱ ለኮሚሽኑ ይሆናል፣

፬/ በመንግሥት መሥሪያ ቤቶች እና በመንግስት ልማት ድርጅቶች ውስጥ የሥነ-ምግባር መከታተያ ክፍል ኃላፊ ወይም ሠራተኛ የመመደብ፣ የመቅጠር፣ የማዛወር እና የማሰናበት ተግባር የኮሚሽኑ ይሆናል፡፡ የሚደራጁት የስነ-ምግባር መከታታያ ክፍሎች ስራ ደረጃ በመንግስት መስሪያ ቤቶች ወይም በመንግስት ልማት ድርጅቶች በሚገኙ ዓላማ ፈጻሚዎች የስራ ደረጃ ጋር ትይዩ ይሆናል፣

2/ The Commission's books of accounts and financial documents shall be Audited annually by the Federal Auditor-General.

## PART THREE
## ESTABLISHMENT OF ETHICS LIAISON OFFICES AND RELATIONSHIP OF THE COMMISSION WITH REGIONAL ETHICS AND ANTI-CORRUPION COMMISSION

### 20. Establishment of Ethics and Anti-Corruption Liaison Offices

1/ The Commission shall establish Ethics and Anti-corruption Liaison offices at every level of Public Offices and Public Enterprises the duty of which shall be to coordinate and carry out ethical issues and corruption prevention activities in their respective office or enterprise;

2/The Commission shall cause the establishment of Ethics and Anti-corruption Liaison offices at every level of Public Organizations the duty of which shall be to coordinate and carry out ethical issues and corruption prevention activities in their respective organization;

3/ The ethics and anticorruption Liaison office shall be accountable to the Commission;

4/ It shall be the duty of the Commission to assign, employ, transfer and dismiss the head or employee of the ethics and anticorruption liaison offices of public offices and enterprises. The ethics liaison offices to be established shall be organized in parallel with the line staff of the public offices or enterprises;

፭/ ኮሚሽኑ በህዝባዊ ድርጅቶች ውስጥ የሥነ-ምግባር መከታተያ ክፍል ኃላፊ ወይም ሠራተኛ እንዲመደብ፣ እንዲቀጠር፣ እንዲዛወር እና እንዲሰናበት ያደርጋል፡፡ የሚደራጁት የስነ-ምግባር መከታታያ ክፍሎች የስራ ደረጃ በህዝባዊ ድርጅቶች በሚገኙ ዓላማ ፈጻሚዎች የስራ ደረጃ ጋር ተያዩ ያሆናል፤

፮/ በመንግሥት መሥሪያ ቤቶች፣ በልማት ድርጅቶች እና በህዝባዊ ድርጅቶች ውስጥ የሚደራጁት የሥነ-ምግባር መከታታያ ክፍሎች ከኮሚሽኑ ጋር የሚኖራቸውን የሥራ ግንኙነት፣ አደረጃጀት እና አሰራር ኮሚሽኑ በሚያዘጋጀው መመሪያ ይወሰናል፤

፯/ የሥነምግባርመከታታያክፍሎች ከሚደራጁበት የመንግሥት መሥሪያ ቤት፣ የልማት ድርጅት እና የህዝባዊ ድርጅቶች ጋር የሚኖራቸውን የሥራ ግንኙነት ኮሚሽኑ በሚያዘጋጀው መመሪያ ይወሰናል፡፡

፳፩. ኮሚሽኑ ከክልል የስነ-ምግባርና የፀረ ሙስና ኮሚሽኖች ጋር ስለሚኖረው የሥራ ግንኙነት

፩/ ኮሚሽኑ በሀገር ደረጃ የስነ-ምግባር እና የፀረ ሙስና ተግባራትን የመምራት እና የማስተባበር ተግባራትን የሚያከናውን ስለሆነ የክልል እና የከተማ አስተዳደሮች የሥነምግባር የፀረ ሙስና ኮሚሽኖችን ያስተባብራል፤ የቴክኒክ ድጋፍ ያደርጋል፤

፪/ ኮሚሽኑ ከክልል እና ከከተማ አስተዳደር የሥነ-ምግባርና የፀረ ሙስና ኮሚሽኖች ጋር የእቅድ፣ የሪፖርት እና የግንኙነት ስርዓት ይፈጥራል፤

5/ The Commission shall cause the assignment, employment, transfer and dismissal of the head or employee of the ethics and anticorruption Liaison offices of public organizations. The ethics liaison offices to be established shall be organized in parallel with the line staff of the public organization;

6/ Particulars regarding the ethics and anticorruption Liaison office's work relation with the Commission, their organization and operation shall be specified by directives to be issued by the Commission;

7/ The work relation of the ethics Liaison offices with their respective public office, public enterprise or public organization shall be determined by directives to be issued by the commission.

21. **Work Relations of the Commission with the Regional Ethics and Anti-Corruption Commissions**

1/ The Commission being an organ responsible for leading and coordinating Ethics and Anti-corruption activities at National level shall coordinate Ethics and Anti-corruption commissions of regional and city administrations and give technical support;

2/ The Commission shall establish a planning, reporting and relation system with the Ethics and Anti-corruption commissions of the regional and city administrations;

፫/ የክልል እና የከተማ አስተዳደር የስነምግባርና የፀረ ሙስና ኮሚሽኖች በየአካባቢያቸው ስላለው የፀረ ሙስና እንቅስቃሴ የሚመለከቱ ሪፖርቶችን እና ስታስቲካዊ መረጃዎችን በየጊዜው ለኮሚሽኑ ይሰጣሉ፡፡

## ክፍል አራት
## ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

### ፳፪. የመተባበር ግዴታ

ማንኛውም ሰው ወይም አካል ኮሚሽኑ በዚህ አዋጅ መሰረት የተሰጠውን ስልጣን እና ተግባሩን ለመወጣት በሚያርገው እንቅስቃሴ የመተባበር ግዴታ አለበት፡፡

### ፳፫. ደንብና መመሪያ የማውጣት ሥልጣን

፩/ የህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ለዚህ አዋጅ አፈጻጸም ደንብ ሊያወጣ ይችላል፡፡

፪/ ኮሚሽኑ ይህንን አዋጅና በዚህ አዋጅ መሠረት የሚወጣውን ደንብ ለማስፈጸም መመሪያ ሊያወጣ ይችላል፡፡

### ፳፬. የተሻሩና ተፈጻሚነት ስለማይኖራቸው ህጎች

፩/ በፌዴራል የሥነ-ምግባርና የፀረ ሙስና ኮሚሽን ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር ፬፻፴፫/፲፱፻፺፯ እና በማሻሻያ አዋጅ ቁጥር ፰፻፹፫/፪ሺ፯ ላይ ተደንግገው የነበሩና በዚህ አዋጅ የተሸፈኑ ድንጋጌዎች በዚህ አዋጅ ተሽረዋል፡፡

፪/ ከዚህ አዋጅ ጋር የሚቃረኑ ማናቸውም ሌሎች ህጎች በዚህ አዋጅ ውስጥ በተሸፈኑ ጉዳዮች ላይ ተፈፃሚነት አይኖራቸውም፡፡

3/ The City and Regional Ethics and Anti-corruption commissions shall submit statistical data and periodic report regarding the state of anti-corruption activities in their respective City or Region to the Commission.

## PART FOUR
## MISCELLANEOUS PROVISIONS

### 22. Duty to Cooperate

Any person is duty bound to cooperate whenever cooperation and assistance is required by the Commission in connection with its powers and duties.

### 23. Powers to Issue Regulations and Directives

1/ The House of Peoples Representatives may issue Regulations for the implementation of this Proclamation;

2/ The Commission may issue Directives for the implementation of this Proclamation and the Regulations issued under this Proclamation.

### 24. Repealed and Inapplicable Laws

1/ Provisions provided under The Revised Federal Ethics and Anti-Corruption Commission Establishment Proclamation No.433/2005 and Amendment Proclamation No. 883/2015 covered by this Proclamation are hereby repealed;

2/ All laws which are inconsistent with this Proclamation shall not apply on matters covered under this Proclamation.

፳፭. አዋጁ የሚፀናበት ጊዜ

ይህ አዋጅ በፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡

አዲስ አበባ የካቲት ፲፪ ቀን ፪ሺ፲፫ ዓ.ም

**ሳህለወርቅ ዘውዴ**
**የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ፕሬዚዳንት**

## 25. Effective Date

This Proclamation shall enter into force as the day of its publication on Fede Negarete Gattee .

**Done at Addis Ababa, On this 19th Day February, 2021.**

**SAHLEWORK ZEWDIE**
**PRESIDNET OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA**

ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ድርጅት